# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 345 ታህሳስ 10 2007


ወያኔ ዛሬ ከመቸውም በበለጠ ነቅዞል። የጭካኔውና የፍርሀቱ ምንጪ ጣር ሞቱ እንጂ ሌላ አይደለም።

ሞትና ህይወትን ከሚያማርጥ ስደት የደረሰው ወጣቱ አርበኝነትን መምረጥ አለበት። ከቀን ጅቦች ራስን በማዳን ውርደትን፣ ስደትን ማስወገድ ይቻላል። ይህ የነገ ሳይሆን የዛሬ ውሳኔ መሆን ይኖርበታል።

በመሆኑም ግንቦት 7 ወጣቱ በያለህበት በራስህ አነሳሽነት እንድትደራጅ ያበረታታል። ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በኢትዮጵያ ያለው አስከፊ ጭቆና በአገሪቱ ላይ የታለመውን ዕድገት ፈጽሞ እንደማያመጣ ተገለጸ

*በኢትዮጵያ ከጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ጋር የተቆራኙትን ጥቂቶችን ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ ስርአት መኖሩም ተመልክቷዋል።*

በኢትዮጵያ ውስጥ የተንሰራፋው የዴሞክራሲ እጦት፤ ጭቆናና አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት ገዥው ፋሺስታዊ ቡድን ተያይዣዋለሁ የሚለውን የእድገት ጉዞ ያቀጭጨዋል ሲሉ አንድ ተቀማጭነታቸውን በደቡብ አፍሪካ ያደረጉ ምሁር አስጠንቅቀዋል። ፍትሐዊ የሃብት ክፍፍል በሌለባት በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ባለ ቢሊየነሮቹና ሚሊየነር ሐብታሞቹ ሰፊው ህዝብ ሳይሆን ጥቂቶቹ ከአገዛዙ ጋር የተጠጉትና የተሻረኩት ብቻ ናቸው ሲሉ ተናግረዋል። የዲሞክራሲ መሰረታዊ ክንዋኔዎች በሚል ስያሜ በሚታወቀው ተቋም ሊቀመንበር የሆኑትና የበርካታ መጽሃፍት ጸሃፊ የሆኑት ዊሊያም ጎንዴ ደቡብ አፍርካ ውስጥ ለሚታተመው የአገሪቱ ታላቅ ጋዜጣ ዘ ሰንደይ ኢንዲፔንደንስ ባቀረቡት ኢትዮጵያ ተኮር ሰፊ ዘገባቸው አገሪቱ ከዛሬ 30 አመታት በፊት ከምትታወቅበት የረሃብና የእርዛት አገርነት ለመውጣት ብትንገዳገድም በአገሪቱ የተንሰራፋው እውነተኛ የዲሞክራሲ እጦት እና ዜጎች ሃሳባቸውን በነፃነት እንዳይገልጹ የሚደረገው አፈናና ጭቆና የታለመውን እድገት ፈፅሞ እውን አያደርገውም ብለዋል። የኢትዮጵያ እድገት ተአምር ወይስ የማይጨበጥ ጉም በሚል አርዕስት ጥናታዊ ጽሁፋቸውን በጋዜጣው ያቀረቡት ሚስተር ዊሊያምስ በኢትዮጵያ ውስጥ የኢኮኖሚው እድገት ተጠቃሚዎች ሰፊው ማህበረሰብ ሳይሆን ለአገዛዙ ያደሩ ጥቂት ግለሰቦች መሆናቸውን በማመልከት፤ ለማስረጃነትም ከ 2007 እ.ኤ.አ እስከ አለፈው አመት ድረስ ኒው ወርልድ ሄልዝ የተባለ ተቋም ያካሄደውን ጥናት ዋቢ በማድረግ ያቀረሰቡ ሲሆን ሚስተር ዊሊያምስ በስተመጨረሻም በአገሪቱ ለተንሰራፋዊ ኢፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል ጉጅሌዎቹ ተጠያቂ መሆናቸውን በመጠቆም በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ትችት ሰንዝረዋል። ... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የግንቦቱን የምርጫ ድራማ ተከትሎ የወያኔ ሹማምንት ካሁኑ መበላላት ጀምረዋል

ወያኔ አገዛዝ በመጭው ግንቦት ወር ሊካሄድ ቀጠሮ የተያዘለትን ምርጫ ተከትሎ በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ እየተቸራቸው፤ ሰፊ ተቀባይነት ባያገኙት የተቃዋሚ ሃይሎች አመራርና አባላት እንዲሁም ደጋፊዎች ላይ እየወሰደ የሚገኘው አረመኔያዊ ድብደባ፤ ወከባና የጅምላ እስር እርምጃ በቱባ ሹማምንቱ መካከል አለመግባባት መፍጠሩን የውስጥ ምንጫችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል። የምርጫ ጊዜው መቃረቡን ተከትሎ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ የሚገኘው ፋሺስታዊ አገዛዝ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ከፍተኛ ማስፈራሪያና ሽብር እነዛ ለማሽማቀቅ ብሎም ከምርጫው ውድድር ውጭ ለማድረግ ጥረት እያደረገ ቢሆንም በተቃዋሚዎች በኩል እየታየ ያለው አልበገርም ባይነትና ለትግሉ እስከ ህይወት መስዋዕትነት የመክፈል ዝግጁነት ቱባ ሹማምንቱን ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ከቷቸው እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል።በተለይ የጉጅሌው ወያኔ የተቃዋሚ ሃይሎችን ለማስፈራራትና ለማሽማቀቅ በሚል የመረጠው እንቅስቃሴያቸውን ተቀማጭነታቸውን በውጭ ካደረጉ ሃይሎች ጋር በማያያዝ የመወንጀል ሴራ የማያዋጣ መንገድ መሆኑን የሚናገሩ ቱባ ሹማምንት እየተበራከቱ መምጣታቸውም ታውቋል። መጭውን የግንቦት ወር ምርጫ በተመለከተ በጉጅሌው ወያኔ ሹማምንት ውስጥ እየተከሰቱ ያሉት የአካሄድ ልዩነቶች በአመራሮቹን መካከል አለመተማመንን እያሰፈኑ ከመሆኑም የያዝነው የአፈናና የጭቆና መስመር አያዋጣም!? እስከመቼስ እንዲህ ይቀጥላል? የሚሉ አመራሮች ከመካከላቸው እየተነሱ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል።

በተያያዘ ዜና የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ መጭውን የግንቦት ወር ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል በጀት ባለመኖሩ የአገዛዙ ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንደሚገኝ ታውቋል። ... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## ኢትዮጵያ ዉስጥ ስዊድን ዜጎች ላይ የተደረገው የግድያ ሙከራ የስዊድን መንግስትን አስቆጣ

ሰሞኑን በኦሞ ስምጥ ሸለቆ ለሽርሽር በሄዱት በኢትዮጵያ የስዊድን አምባሳደርን ጨምሮ ሌሎች 12 ስዊድናውያን ላይ ከፍተኛ የተኩስ እሩምታ በመክፈት የተደረገው የመግደል ሙከራ የስዊድን መንግስትን ማስቆጣቱን ታወቀ። በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ የተሰነዘረ ጥቃት ሳይሆን እንደማይቀር በስፋት በተነገረለት በዚህ የመግደል ሙከራ፤ በሁለቱ አገሮች መካከል ባለው ዘላቂ ግንኙነት ላይ አደጋ ጋርጦበት እንደሚገኝ ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ የውስጥ ምንጮቻችን አስታውቀዋል። የተሰነዘረውን የመግደል ሙከራ የስዊድን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲሁም ጥቂት የማይባሉ የስዊድን መገናኛ ብዙሃን ሰፊ ሽፋን በመስጠት ጉዳዩን መዘገባቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የመገናኛ ብዙሃኑ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጎቻቸው ከፍተኛ አደጋ ተጋርጦባቸው እንደሚገኝ በመጠቆም መንግስት ከፍተኛ ጥንቃቄ መውሰድ መጀመር እንደሚኖርበት አጥብቀው ማሳሰባቸው ታውቋል። ጉዳዮን የስዊድን መንግስት በቸልተኝነት እንደማይመለከተው በማሳሰብ፤ ድርጊቱ እንዴትና በማን እንደተፈጸመ ጥናት በማድረግ መንግስት ተመጣጣኝ እርምጃ ለመውሰድ ዝግጅት መጀመሩን የስዊድን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማስታወቁን ምንጮቻችን አስታውቀዋል። ይሁን እንጂ ጉዳይ በተመለከተ የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንትም ሆኑ አገዛዙ እንዳሻው የሚቆጣጠራቸው ራድዮ እና ቴሌቪዥን እስካሁን ምንም ያሉት ነገር እንደሌለ ለማወቅ ችለናል። ... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች በሸንሌ ዞን 7 ሰዎችን በጥይት ደብድበው መግደላቸው ተዘገበ

በሽነሌ ዞን በአፋርና በኢሳ መካካል ያለውን የቆየ የድንበር ውዝግብ ተከትሎ የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ የተወሰኑ ቦታዎችን ወደ አፋር ክልል እንዲካተቱ መወሰኑን ተከትሎ በተነሳ ህዝባዊ ተቃውሞ 7 ሰዎች በአገዛዙ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች በጥይት ተደብድበው ሲገደሉ ቁጥራቸው ከ30 በላይ የሚሆኑት ደግሞ ከባድ የመቁስል አደጋ እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሏል። በአካባቢው እየተደረገ ያለው ህዝባዊ ተቃውሞ ከዕለት ዕለት እየተባባሰ መሄዱን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ከሁለቱም ጎሳዎች ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሰዎች ታፍሰው ወደ አልታወቀ እስር ቤት መጋዛቸው ታውቋል። ከህዝባዊ ተቃውሞ ጋር በተያያዘ በአካባቢው አሁን ድረስ ከፍተኛ ውጥረት የሰፈነ ሲሆን፣ የአካባቢው ነዋሪዎች ነነቂስ ወጥተው አገዛዙን የሚያወግዙ የተቃውሞ ሰልፎችንም እያደረጉ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል።

## በከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ የተገዙ የማምረቻ መሳሪያዎች በኤሌክትሪክ ሃይል ችግር ከአገልግሎት ውጭ ሆኑ

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የዉጭ ምንዛሬ እየከፈለች ኩወጭ አገሮች የምታስመጣቸዉ የማምረቻ መሳሪያዎች አገር ዉስጥ በሚታየዉ የኤሌክትሪክ እጥረት የተነሳ ምንም ጥቅምና አገልግሎት ሳይጡ ቆመዉ መቅረታቸዉን የውሃ፣ የመስኖና የኢነርጂ ሚኒስትሩ አለማየሁ ተገኑ ተናገረ። አለማየሁ ተገኑ ህዳር 26 ቀን 2007፣ በቁጥር ውመአሚ 1/01/67 በጻፈዉ ደብዳቤ" በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በከፍተኛ ወጪ ተገንብተው ለበርካታ ኢንተርፕራይዞች የመስሪያና መሸጫ አገልግሎት የሚውሉ ህንጻዎችና በኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ችግር ምክንያት ለታለመላቸው አላማ ለማዋል" አልተቻለም ብሏል።

"በእነዚህ ማእከላት ውስጥም በከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ የገቡና ሊገቡ የተሳቡ የማምረቻ ማሽነሪዎች ምርትን ማምረት አልቻሉም" ያሉት ሚኒስትሩ፣ "በሃይል አቅርቦት እጥረት ምክንያት ከግብርናው ወደ ኢንዱስትሪው ለሚደረገው ሽግግር ወሳኝ የሆነውን የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን ወደ ተግባር በማስገባት በሚፈለገው ደረጃ ለማፋጠን አልተቻለም" ሲሉ አክለዋል።አቶ አለማየሁ ችግሩን ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ይደረጋል ቢሉም፣ ችግሩ የሚፈታበትን የጊዜ ገደብ አላስቀመጡም። የሃይል አቅርቦት ችግሩ መንስኤ ምን እንደሆነም አልጠቀሱም።በአገር ውስጥ የሚገኙ የግልና የመንግስት የማምረቻ ተቋማት በኤሌክትሪክ ሃይል እጥረት ስራቸውን ለማከናወን እየተቸገሩ ባለበት ወቅት፣ መንግስት የኤሌክትሪክ ሃይል ለጎረቤት አገሮች በማቅረብ ላይ መሆኑን ይናገራል።

## የወደፊቱ የተሻለ የህይወት ተስፋ ያለው ወያኔ መቃብር ላይ ነው!!

ወያኔ በሀገራችን የዘረጋው ማህበራዊ ፖለቲካዊና የኢኮኖሚ ስርአት ለጠቅላላ ህዝባችን፣ በተለይ ለወደፊቱ ሀገር ተረካቢ ወጣት ሲኦል መሆኑ ቅጥሏል። በሀገሬ ውስጥ፣ ሰርቸ የተሻለ ህይወት እኖራለሁ ብሎ ማለም ቅዠት ሆኗል። ከዚህ ይልቅ ያብዛኛውን ወጣት ተስፋ ሀገር ጥሎ በገፍ መሰደድ ከሆነ ውሎ አድሯል።

በእጅጉ በሚዘገንን ሁኔታ በግፍ ተሰቃይተው ከሳውዲ አረቢያ ወደሀገራቸው ከተመለሱት ከ160 ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን ግማሽ ያህሉ ተመልሰው መሰደዳቸውን በቅርቡ የወጣ ጥናት አረጋግጦል። በዚህ ሁኔታ ከተሰደዱ ወገኖቻችን ውስጥ ቁጥራቸው ከ70 በላይ የሚሆኑት ቀይ ባህር ላይ የነበሩበት ጀልባ ሰምጦ አልቀዋል። እነዚህ ወገኖቻችን ጉዞቸው በሞትና ህይወት መሃል መሆኑን አስቀድመው ያውቃሉ። ይህንን ያስመረጣቸው ግን የወያኔ ስርአት ነው። የወያኔ ስርአት የተመቻቸው ለስርአቱ ሹመኞችና ለዘመድ አዝማድ ከዚያ ከተረፈ ለጎሳ ተወላጆቻቸው ብቻ ነው። ሀገሪቱ ውስጥ ተገኘ የሚባል የኢኮኖሚ እድገት ካለም ከዚሁ ከጠባብ ቡድን ጥቅም አልፎ መከረኛውን ህዝብ የሚጠግን አልሆነም።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ከተስፋ ቆራጪነትና ሞትና ህይወትን ከሚያስመርጥ አስከፊ ህይወት ያለፈ ምርጫ አለ። ዋናው ምርጫቸውም ይህ ሊሆን ይገባል፤ ምርጫው ለዚህ መከራና ሀዘን ውርደት የዳረገንን ጨካኝ የወያኔ ስርአት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገድ ነው።

ወያኔ የህዝቡ ጉስቁልናና ስቃይ ጉዳዩ አለመሆኑን ባለፉት ሳምንታት ከ70 በላይ ወገኖቻችን ቀይ ባህር ውስጥ ሰምጠው: አለም በሀዘን በሚመለከተንና መንግስት አለ ብሎ የሀዘን መግለጫ በሚልክበት ሰአት የብሄረሰብ ቀን በሚባል የቦልት በአል የወያኔ ሹሞች ብዙ ሚሊዮን ብር አውጥተው በውስኪ እየተራጩ ይጨፍሩ ነበር።

ይህ አልበቃ ብሎ አሻንጉሊቱ ሃይለማርያም ደሳለኝ በስደተኛው ላይ ለሰሚ የሚቀፍ የወረደ አሉባልታና ስድብ ሲያወርድ ሰምተናል፣ ራሱን ያወረደ ተረት ተረትም ተናገረ። በሥልጣን የመባለግ ዝንባሌያቸው ሳይውል ሳያድር በሚጠቀሙት የባለገ አዋራጅ ቃላት የመጠቀም ርሃባቸው አሳየን።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ፡-

በምድረ ኢትዮጵያ የተስፋ መቁረጥና ለወያኔ ሎሌዎቹ መሳለቂያ እንድንሆን ያበቃን ይህ የነቀዘ ዘራፊ የወያኔ ስርአት ብቻ ነው። ይህ ሁሉ ስቃይና ውርደት የሚቆመው ወያኔ ሲወገድ ብቻ መሆኑን ሁላችንም ጠንቅቀን ልንረዳ ይገባል። በቅርቡ ዱላውንና ግፉን ሁሉ ለመቀበል ቆርጠው ወያኔን ከተጋፈጡት የሰማያዊ ፓርቲ አባልና ደጋፊ ወጣቶች ብዙ ልንማር ይገባል። እንደአባብ በጭካኔ መቀጥቀጣቸው አጠነከራቸው እንጂ አላዳከማቸውም።

ወያኔ ዛሬ ከመቸውም በበለጠ ነቅዞል። የጭካኔውና የፍርሀቱ ምንጪ ጣር ሞቱ እንጂ ሌላ አይደለም።

ሞትና ህይወትን ከሚያማርጥ ስደት የደረሰው ወጣቱ አርበኝነትን መምረጥ አለበት። ከቀን ጅቦች ራስን በማዳን ውርደትን፣ ስደትን ማስወገድ ይቻላል። ይህ የነገ ሳይሆን የዛሬ ውሳኔ መሆን ይኖርበታል።

በመሆኑም ግንቦት 7 ወጣቱ በያለህበት በራስህ አነሳሽነት እንድትደራጅ ያበረታታል። አመች ሁኔታ ያለህ ወጣት ደግሞ ተቀላቀለን። ሰራዊቱ ውስጥ ያለህ ወጣትና ሎሌነት የሰለቸህ ሁሉ የነጻነት ሀይሎችን ትቀላቀል ዘንድ ጥሪያችን ይድረስህ።

የሀገራችን የህዝባችንና የያንዳንዳችን የተሻለ ህይወትና ዘመን ተስፋ የተቀመጠው ወያኔ መቃብር ላይ መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !**

---

## ማህበረ ቅዱሳን ውስጥ ግንቦት 7ቶች ፣ ፕሮቴስታንቱ ዉስጥ ደግሞ የኦነግ ሰዎች አሉ - ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም

በቅርቡ የፌደራልና የክልል የጸጥታ ዘርፍ ሃላፊዎች በባህርዳር በተሰባሰቡበት ወቅት የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር የሆኑት ዶ/ር ሽፈራው ተ/ማርያም ፣ ይህን የተናገሩት የሃይማኖት ተቋም የፖለቲካ ፍላጎት ማራመጃ መሆኑን ለማስረዳት ነው። ዶ/ር ሽፈራው ከአፋር የጸጥታ ዘርፍ ሃላፊ " መንግስት ለምን በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ይገባል? ለምንስ በአገራችን የሌለ ችግር ያመጣብናል?" በሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። ዶ/ር ሽፈራው ይህንን ለማስረዳት ይጠቅማል ያሉዋቸውን ምሳሌዎች አቅርበዋል። በጥቅምቱ የሲኖዶስ ጉባኤ የኢሳት ሬዲዮና ቴሌቪዥን የሲኖዶሱን ውሎ በእየለቱ ሲዘግብ የነበረው በማህበረ ቅዱሳን ውስጥ በሚገኙ አባላት አማካኝነት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ግንቦት7 እና ኢሳት ሃይማኖትን ለፖለቲካ እምነት ማራመጃ ለመጠቀም እንደሚፈልጉ ዋናው ማሳያ ነው ሲሉ ደምድመዋል።

ፕሮቴስታንት ሃይማኖት ለኦነግ አላማ ማስፈጸሚያ እያገለገለ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፣ ኦነግ ከፕሮቴስታንት አልፎ ዋቄ ፈታንም እየተጠቀመ ነው ብለዋል አክራሪነት ስልቱን ቀየረ እንጅ አልተሸነፈም ያሉት ዶ/ር ሽፈራው፣ በሚቀጥሉት ወራት በሃይማኖት ተቋማት ላይ፣ በትምህርት ቤቶች፣ በወጣትና ሴቶች ማህበራት ሰፊ ዘመቻ እንዲጀመር መክረዋል። በተለይ አዲስ አበባ ስራዎች ቢሰሩም ተመልሶ ማጥ የሚገቡበት በመሆኑ፣ የአዲስ አበባ መዋቅራችን አክራሪነትን አሸነፍኩ ብሎ ሊዘናና እንደማይገባው አሳስበዋል።

ማህበራዊ የመገናኛ ብዙሃን በተለይም ፌስቡክና ትዊተር ትልቅ ችግር እየፈጠሩ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ እነዚህን የመገናኛ ብዙሃን ለመጠቀም እቅድና ስትራቴጂ ተነድፎ በሙሉ ጊዜና ሃይል የሚሰራ ሰው መድቦ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህን ተግባራዊ ማድረግ የትግሉ ዋናው አካል መሆን ይገባዋል ብለዋል።

መጪውን ምርጫ በተመለከተ በሁዋላ ላይ ችግር ሳይፈጠር ከአሁኑ እርምጃዎችን በመውሰድ መንቀሳቀስ እንደሚገባም አክለዋል። በአገሪቱ ያሉ የጸጥታ ሃይሎች በምርጫው ላይ መውሰድ ስለሚገባቸው እርምጃም ውይይት አድርገዋል። የውውይቱ ውጤት እንደደረሰን ለህዝብ የምናቀርብ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ማህበረ ቅዱሳን ከቀኖና ጋር በተያያዘ ለመክሰስ የተዘጋጁ የደህንነት መስሪያ ቤት ያደራጃቸው ሰዎች ምክክር እያደረጉ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል። ሰዎቹ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ስልጠና እየወሰዱ ሲሆን፣ ከተወሰኑ ጊዜያት በሁዋላ በማህበረ ቅዱሳን ላይ በሃሰት በመመስከር ማህበረ ቅዱሳን የእኛ ነው በሚል ነባሩን ድርጅት ለማሳገድ እና ለገዢው ፓርቲ ተለጣፊ የሆነ ማህበረ ቅዱሳን ለማቋቋም እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ምንጮቻችን ገልጸዋል። በማህበረ ቅዱሳን ስም ማህተም ከማስቀረጽ ጀምሮ የተለያዩ ህገደንቦችን እያረቀቁ መሆኑን ምንጮች አክለው ገልጸዋል።

## በኢትዮጵያ ያለው አስከፊ ጭቆና በአገሪቱ

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዘራፊው የወያኔ አገዛዝ የስልጣን ላይ ቆይታውን ለማርዘም አገሪቱን በመጭው የፈረንጆች 2025 ኢ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ እሰራለሁ የሚል ዲስኩሩን ራሱ እንዳሻው በሚዘባርቅበት ቴሌቭዥን ሌት ተቀን እያስተጋባ እንደሚገኝ የሚታወቅ ሲሆን ሚስተር ዊሊያምስ በዚህ ዙሪያ አስተያየታቸው ሲሰነዝሩ ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል በሌለበት አገር ይህ ፈጽሞ የማይታሰብ ቅዥት መሆኑን ተናግረዋል። በአለም ባንክ መስፈርት መሰረት እንደ አንድ አገር የመካከለኛ ገቢ አላት ለመባል የህዝቡ የነፍስ ወከፍ አመታዊ ገቢ ከ 1430 የአሜሪካ ዶላር መሆን ይገባዋል ያሉት ዊሊያምስ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት የህዝቧ አመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ 470 የአሜርካን ዶላር በታች መሆኑን በማመልከት ይህም ኢትዮጵያን ከአለማችን ደሃ አገሮች ተርታ ለመካተት ግድ ብሏታል ሲሉ ሃሳባቸው ሰንዝረዋል።

## ኢትዮጵያ ዉስጥ ስዊድን ዜጎች ላይ የተደረገው የግድያ

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ እንደተቃጣ እየተነገረ በሚገኘው 12ቱ ስዊድናውያንን የመግደል ሙከራ ጉዳይ በቅርቡ የስዊድን የጦር ፍርድቤት ኢትዮጵያውያን በ 13 የጉጅሌው ወያኔ ሹማምንት ላይ ያቀረቡትን የወንጀል ክስ ተቀብሎ ክስ እንደሚመሰርት ማስታወቁ አገዛዙን አስቆጥቶት የሰነዘረው የአጸፋ እርምጃ ሳይሆን እንደማይቀር በበርካታ ኢትዮጵያውያን ዘንድ እየተነገረ እንደሚገኝ ታውቋል። በ13 የጉጅሌው ወያኔ ሹማምንት በምርጫ 97 ወቅት በንጹሃን ዜጎች ላይ ለፈጸሙትና ላስፈጸሙት ግድያና እስር እንዲጠየቁ ኢትዮጵያውያን ያቀረቡት ክስ የስዊድኑ አለማቀፍ የጦር ወንጀለኞች ፍርድ ቤት ክሱን ተቀብሎ ምርመራ ለማድረግ መወሰኑ በተለያዩ ሚዲያዎች መዘገቡ ይታወሳል። የወንጀል ክሱ ሲጠናቀቅና ሹማምንቱ ጥፋተኝነታቸው ሲረጋገጥ ጉጅሌዎቹ በየትኛውም አገራት ቢዘዋወሩ ተይዘው ለፍርድ እንደሚቀርቡ ታውቋል ይህ ውሳኔ ፍትህ ለተነፈጉ ኢትዮጵያውያን ተስፋ ሰጭ እንደሆነ በስፋት ተነግሯል።

---

# ሞትን ሸሽቶ ተራ ሞት ከመሞት ከገዳዮች ጋር ተፋልሞ በክብር መሞት የኢትዮጵያዊነት ምልክት ነዉ

ወጣቱ ትዉልድ በየትኛዉም አገር ወይም ህብረተሰብ ዉስጥ በአገር ልማት'፤ በመሰረታዊ ተቋሞች  ግንባታና አገርን በመከላከል ስራዎች ላይ የተሸከመዉ ኃላፊነት ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች የበለጠ ነዉ። እንደ ኢትዮጵያ አይነት ዘረኛ አምባገነኖች በነገሱበት አገር ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት አገራዊ አደራና ሀላፊነቶች በተጨማሪ ወጣቱ ትዉልድ እራሱንና ወገኖቹን ከዘረተኝነትና ከአምባገነንነት አላቅቆ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት የመገነባት ተጨማሪ ሀላፊነት አለበት። ወጣቱ ትዉልድ የኢትዮጵያን አገራዊ ራዕይ የተሸከመ ደከመኝን የማያዉቅ ተከታታይነት ያለዉ የማይነጥፍ የህይወት ምንጭ ነዉ። በእርግጥም ወጣትነት የህይወት ህልምና ፊቺዉ አብረዉ የሚገለጹበት የእድሜ ክልል ነዉ። ወጣቱ ደግሞ ራዕይ ተሸካሚ ብቻ ሳይሆን የተሸከመዉን ራዕይ እዉን ሆኖ ለማየትና ለማሳየት ብቃቱ፤ ችሎታዉና ፍላጎቱ ያለዉ መበአካሉም በመንፈሱን ጠንካራ  የሆነ  የህብረተሰብ ክፍል ነዉ።

አገራችን ኢትዮጵያ በአለም ታሪክ ዉስጥ እንደ አገር ተመዝግባ በኖረችባቸዉ ረጂም አመታት ዉስጥ የየዘመኑ ወጣት ለእናት አገሩ ሠላም፤ ብልጽግናና የግዛት አንድነት መከበር ይህ ነዉ ተብሎ በቃላት ሊነገር የማይችል ትልቅ መስዋዕትነት ከፍሏል ዛሬም እየከፈለ ነዉ። ትናንት በአባቶቻችን ዘመን የአገራቸዉን ዳር ድንበር በጠላት አናስደፍርም ብለዉ ጫካዉንና ዱሩን ቤታቸዉ ያደረጉ በላይ ዘለቀን፤ አብዲሳ አጋንና ጃገማ ኬሎን የመሳሰሉ ወጣቶች ነበሩን። በ1970ዎቹ ደግሞ ሰዉ በላዉን የደርግ ስርዐት ፊት ለፊት ተጋፍጠዉ ለእናት አገራቸዉ ኢትዮጵያ የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ነበሩ። ዛሬም ዘረኛዉን የወያኔ ስርዐት ለማስወገድና አገራቸዉ ኢትዮጵያን የእኩሎች አገር ለማድረግ በየቀኑ የአካልና የሕይወት መስዋዕትነት የሚከፍሉ ኢትዮጵያዉያን ወጣቶች ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ለምሳሌ በ1997 ዓም የህዝብ ድምጽ ይከበር ብለዉ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ያቀረቡ ከሁለት መቶ በላይ ወጣቶች የጦር ሜዳ መሳሪያ ከታጠቁ አግዓዚ ነብሰ ገዳዮች ጋር ባዶ እጃቸዉን ተጋፍጠዉ በክብር ተሰዉተዋል።

ከላይ ከፍ ሲል አጽንኦት ሰጠተን እንደገለጽነዉ ወጣቱ ትዉልድ የህብረተሰብ አንቀሳቃሽ ሞተር ነዉ። ሀኖም ሞተር ከራሱ ዉጭ ሌሎችን ማንቀሳቀስ የሚችለዉ መጀመሪያ እሱ እራሱ መንቀሳቀስ ሲችል ነዉ። የኢትዮጵያም ሆነ የማንኛዉም አገር ወጣት ሞተር ሆኖ የሚኖርበትን ህብረተሰብ ማንቀሳቀስ እንዲችል ከፍተኛ የመንግስትና የሁሉም ህብረተሰብ ያላሰለሰ ድጋፍ ያስፈልገዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ወጣቱ በነጻነት መንቀሳቀስ የሚችልበት የፖለቲካ፤የማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ድባብ ያስፈልገዋል። እዚህ ላይ አንድ እጅግ በጣም የሚያሳዝነንና የሚያሳስበን ጉዳይ አለ፤ እሱም የኢትዮጵያ ወጣት የእድገት ሞተር ሆኖ አገሩን የሚያንቀሳቅስበት ቀርቶ እሱ እራሱም የነጻነት አየር የተነፈሰበት አንድም የታሪክ አጋጣሚ የለም። በተለይ በወያኔ ስርዐት ዉስጥ ከልጅነት ወደ ወጣትነት የተሸጋገረዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ አገር፤ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት ከሚባሉ ትልላቅ ብሄራዊ እሴቶች ጋር እንዳይተዋወቅ ተደርጎ ያደገ ወጣት ነዉ።

የዛሬዉ ዘመን ኢትዮጵያዊ ወጣት በጻፈ ቁጥር የሚደበደብ፤ ባነበበ ቁጥር የሚጋዝ፤ ተናግሮ ሀሳቡን በገለጸ ቁጥር ደግሞ ከየመንገዱ እየተለቀመ የት እንደደረሰ እንኳን ሳይታወቅ ደብዛዉ የሚጠፋ  ቀን የጨለመበት ወጣት ነዉ። ባጠቃላይ ወያኔ ስልጣን ይዞ በቆየባቸዉ ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት  ዉስጥ የኢትዮጵያ ወጣት የአባቶቹን ታሪክ እንዳያዉቅና ከዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ ጋር ሳይተዋወቅ ድቅድቅ ጨለማ ዉስጥ እንዲኖር ተደርጓል። የኢትዮጵያ ወጣት ከመረጃ ቴክኖሎጂ ጋር ተዋዉቆ እራሱን  ካደራጀና ከጓደኞቹ ጋር ባሰኘዉ ግዜ ሁሉ ከተገናኘ በአገሩ የፖለተካና ማህበራዊ መድረኮች ላይ የሚጫወተዉን ሚና ወያኔ ስለሚረዳ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም ከወሰዳቸዉ እርምጃዎች አንዱና ዋነኛዉ ወጣቱ ህብረተሰብ ከመረጃ ቴክኖሎጂ ጋር ያለዉን የቅርብ ግኑኝነት መስበር ነዉ። ይህ ፀረ አገርና ፀረ ዕድገት እርምጃ ደግሞ ወጣቱን ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ አገራችን ኢትዮጵያ በመረጃ ቴክኖሎጂ ዕድገትና ስርጭት የአለማችን የመጨረሻዋ ጭራ አገር እንድትሆን አድርጓታል። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያን ወጣት አማራጭ አሳጥቶ ከዚህ ቀደም ታይቶም ተሰምቶም በማያዉቅ ፍጥነትና ብዛት አገሩን እየጣለ እንዲሰደድ አድርጎታል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና ሌሎችም አለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ያደረጉት ጥናት በግልጽ እንደሚያመለክተዉ ምሁሩና ወጣቱ ትዉልድ በከፍተኛ ቁጥር ከሚሰደድባቸዉ አገሮች ዉስጥ ኢትዮጵያ በዓለዉ ዉስጥ ቀዳሚዉን ቦታ የያዘች አገር ናት። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የኢትዮጵያን አኮኖሚ የአፍሪካ የዕድገት ምልክት አድርገነዋል እያሉ ቢፏልሉም ይህ አሳደግነዉ የሚሉት ኤኮኖሚ ስራ አልባ ኤኮኖሚ በመሆኑ  የራሱን አገር መገንባት የነበረበት ኢትዮጵያዊ ወጣት ወንድ ሴት ሳይል እጅግ በጣም በሚያስፈራ ፍጥነት አገሩን እየለቀቀ በመዉጣት ላይ ነዉ።

ዛሬ በዘለም ዙሪያ ከደቡብ ኮሪያ እስከ አዉስትራሊያ፤ ከሳዑዲ አረቢያ እስከ ካናዳ በየአህጉሩ፤ በየአገሩና በየደሴቱ ላይ ኢትዮጵያዉያን ስደተኞች የሌሉበት አገር የለም። በ1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ የደርግን ጭፍጨፋ እየሸሸ ከአገሩ መሰደድ የጀመረዉ ኢትዮጵያዊ ወጣት ዛሬም ከ37 አመታት በኋላ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ አገዛዝ የለየለት ነብሰ ገዳይ አገፈዛዝ በመሆኑ የኢትዮጵያ ወጣት አሁንም አገሩን እየለቀቀ በመዉጣት ላይ ነዉ። የስደት ጉዞ ብርድና ቁር፤ ሀሩርና ንዳድ፤ እንዲሁም ህመም፤ ቁስልና ሞት የተቀላቀሉት ለወገንም ለባዳም የማይመኙት እጅግ በጣም አደገኛ ጉዞ  ነዉ። ስደት ጉዞዉ ብቻ ሳይሆን ስደተኞች በስደት የሚኖሩበት አገርም ቢሆን ለአካልም ለመንፈስም የማይመች ቦታ ነዉ። ሴቶች እህቶቻችን በየቀኑ ወደ አረብ አገር የሚጎርፉት አካላቸዉ ላይ የፈላ ዉኃ እንደሚደፋ፤ ከፎቅ ላይ እንደሚወረወሩና በአረብ ጎረምሳ በየቀኑ እንደሚደፈሩ እያወቁ ነዉ ከወያኔ ጋር ከመኖር ስደት ይሻላል ብለዉ አገራቸዉን ለቅቀዉ የሚሰደዱት። ወንዶች ወንድሞቻችንም ቢሆኑ የሰሃራን በረሃና የቀይ ባህርን የመከራ ጉዞ ቆርጠዉ የሚገበቡበት ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ ብለዉ ነዉ እንጂ በየበረሃዉና በየባህሩ ላይ እንደወጣ የቀረዉ ኢትዮጵያዊ ቁጥር እጅግ በጣም ብዙ እንደሆነ ሳያዉቁት ቀርተዉ አይለደም። ለመሆኑ ኢትዮጵያዉያን ይህንነ ሁሉ ችግርና ጣጣ እያወቁ ወነድ፤ሴት፤ ወጣት አዛዉንት፤ ሳራተኛና ገበሬ ሳይል ሁሉም በጅምላ እትብታቸዉ የተቀበረበትን አገር እየለቀቁ የሚሰደዱት ለምንድነዉ?

ኢትዮጵያዉያን የሚሰደዱት ወያኔን እየጠሉ ነዉ ወይም የወየኔ ዘረኝነት፤ ከፋትና ጥላቻ እንገፍግፏቸዉ ነዉ ብለዉ የሚገምቱ ብዙ ኢትዮጵያዉያን ሰዎች ሊኖሩ ይቻላል። በጥቅሉ ሲታይ ግምታቸዉ ትክክለኛ ግምት ነዉ፤ የወያኔ ዘረኝነትና ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ብዙ ኢትዮጵዉያንን አንገፍግፏል፤ አበሳጭቷል ወይም አስቆጥቷል። ሆኖም ሰዎች ስለተቆጡና ስለተንገፈገፉ ብቻ እንደ ምፅአት አገራቸዉን እየለቀቁ አይወጡም። ኢትዮጵያዉያን አገራቸዉን እየለቀቁ የሚወጡት ከወያኔ እስር፤ ድብደባና ግድያ ለማምለጥ ነዉ ብለን መገመትም እንችላለን። ትክክለለኛ ግምት ነዉ። ግን ስንቱ ኢትዮጵያዊ ነዉ ኬንያ፤ ማላዊ፤ ሞዛምቢክ፤ ግብፅ' የመንና ሊቢያ ድረስ ሲንከራተት በየመንገዱ እየሞተ ለቀብር እንኳን የማይበቃዉ? ደግሞም የሰዉ ልጅ ባህሪይ የሚያሳድደዉንና የሚገድለዉን እየገደለ መሞት ነዉ እንጂ ሞትን እየሸሰ ጣረ ሞት ዉስጥ መግባት አይደለም። እዉነቱን ለመናገር የኢትዮጵያ ወጣት አገሩን በገፍ እየለቀቀ የሚሰደደዉ የወያኔ ዘረኞች ተስፋዉን ስለገደሉበትና የወደፊቱን ስላጨለሙበት ነዉ።

ተስፋ የሰዉ ልጆች የመኖር ዋስትና ነዉ። እኛ ሰዎች እየከፋንም ቢሆን ደስ እንዳለዉ ሰዉ የምንኖረዉ ይኖረናል፤ ይመቸናል ወይም ከፋዉ ቀን አልፎ መልካም ቀን ይመጣል በሚል ተስፋ ነዉ።ተስፋ የሞተ ቀን ለምን እንደምንኖር ስለማናዉቅ አገር ጥለን መሰደድ ብቻ ሳይሆን ከዚህም የከፋ ብዙ ነገር ማድረግ እንችላለን። ወያኔ ስልጣን ይዞ የቆየባቸዉን ያለፉት ሓያ ሦስት አመታትን ትተን ከ2000 እስከ 2007 ያሉትን ሰባት አመታት ብቻ ስንመለከት ማላዊ ሀይቅ ወስጥ፤ ሰሃራ በረሃ ዉስጥ፤ ኤደን ባህረ ሰላጠና ባቢኤል መንደብ ዉስጥ እጅግ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ኢትዮጵያዊ የአዉሬ ስራት ሆኖ ቀርቷል። ነፃነትና የተሻለ ኑሮ እናገኛለን ብለዉ በኮንቴነር ተጭነዉ ወደ ደቡብ አፍሪካ ይጓዙ የነበሩ ከ50 በላይ ኢትዮጵያዉያን በእግራቸዉ እየተራመዱ ከገቡበት ኮነቴነር እሬሳቸዉ እየተጎተተ ወጥቷል።

ስደትንና እየተሰደደ ደብዛዉ የሚጠፋዉን ኢትዮጵያዊ በተመለከተ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ለጆሮ የሚከብዱ ዜናዎችን ሰምቷል። ባፈዉ ህዳር ወር ማለቂያ ላይ ከወደ የመን የተሰማዉ ዜና ግን ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ብቻ ሳይሆን ለምን ኢትዮጵያዊ ሆኜ ተፈጠርኩ የሚያሰኝ ነዉ። አገራቸዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ወያኔ ተስፋቸዉን ያጨለመባቸዉ አያሌ ኢትዮጵያዉያን እንደ ዜጋ የሚመለከታቸዉና የት ገቡ ወይም የት ደረሱ የሚል መንግስት ስለሌላቸዉ ለቀበር እንኳን ሳይበቁ ቀይ ባህር ዉጧቸዉ ቀርቷል። ለወትሮዉ ለኢትዮጵያዉያን ስደተኞች ብዙም ግድ የሌለዉ የየመን መንግስት እንኳን ሰብዓዊነት ቆርቁሮት ቀይ ባህር እንደዋጠ ያስቀራችዉን ኢትዮጵያዉያን አስከሬን ፍለጋ ጀልባና መርከብ ሲያሰማራ፤ 99 በመቶ ኢትዮጵያዉያን መረጡኝ የሚለዉ የወያኔ አገዛዝ ግን የራሱ ዜጎች ሞት የተመቸዉ ይመስል ሰምቶ እንዳልሰማ ተመልካች መሆኑ አልበቃ ብሎት በተላላኪዉ ጠ/ሚኒስተር በኃ/ማሪያም ደሳለኝ አማካይነት ጭራሽ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ስደተኞችን ሲዘልፍና ሲያጥላላ ከርሟል። አሜሪካ፤ አዉሮፓና መካከለኛዉ ምስራቅ ዉስጥ በየጋዜጣዉ በየቴሌቪዥኑና በማህበራዉ ሜድያዉ የአንድ ሳምንት የመወያያ አርዕስት ሆኖ የከረመዉ የኢትዮጵያዉያኑ እልቀት አገራቸዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ግን ለይስሙላ እንኳን ስማቸዉ አልተነሳም።

አዎ እኛ ኢትዮጵያዉያን የትም እንኑር የት በህይወታችን ቆመንም ሆነ ሞተን ዜጎቼ ብሎ የሚቆረቆረልንና ለወገንና ለአገር ልጅ የሚደረገዉን ልዩ እንክብካቤ የሚየደርግልን መነሰግስ/ት የለንም። አልፎ አልፎ የወያኔ ባለስልጣኖች አዉሮፓና አሜሪካ ሲመጡ በየኤምባሲዉና በሚስጢር በሚያዙ ሆቴሎች ለዉይይት የሚጋብዙት ታማኝ ሎሌዎቻቸዉንና ... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው የተከሰሱት ሰላማዊ ዜጎች በድጋሜ ተቀጠሩ

በእነ ዘላለም ወርቃገኘሁ የክስ መዝገብ የሽብር ክስ የተመሰረተባቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችን ጨምሮ 10ሩም ተከሳሾች የፌደራሉ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ልደታ 19ኛው ወንጀል ምድብ ችሎት ቤት ቢቀርቡም ሌላ ቀጠሮ እንደተሰጣቸው ነገረ ኢትዮጵያ ዘግቧል።

የሰማያዊ፣ የአንድነትና የአረና ፓርቲዎች አመራሮች የሆኑት አቶ የሺዋስ አሰፋ፣ አቶ ሀብታሙ አያሌው፣ አቶ ዳንኤል ሺበሺ እና አቶ አብርሃ ደስታ እንዲሁም አንደኛ ተከሳሽን ጨምሮ ስድስት ተከሳሾች በጠበቆቻቸው አማካኝነት የክስ መቃወሚያቸውን ይዘው ፍርድ ቤት መቅረባቸውን ጋዜጣው ዘግቧል።7ተኛ ተከሳሽ አቶ አብርሃም ሰለሞን የሰጠው የተከሳሽነት ቃል ከክሱ ጋር ተያይዞ ለጠበቃው ባለመቅረቡ ጠበቃው መቃወሚያቸውን እንዲያስገቡ ፍርድ ቤቱ ያዘዘ ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱ የተከሳሾችን የክስ መቃወሚያ መርምሮ ብይን ለመስጠት ለታህሳስ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።

ተከሳሾች በ ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ሊጎበኟቸው የሚሄዱ ቤተሰቦቻቸውና ወዳጆቻቸው ወደ እስር ቤቱ ሲገቡ በተለየ መዝገብ እንዲመዘገቡ በማድረግ ለማሸማቀቅ እየሞከሩ መሆኑን የተናገሩ ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱም አቤቱታውን ተቀብሎ በቀጣይ ቀጠሮ የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ስለጉዳዩ ቀርቦ እንዲያስረዳ ትዕዛዝ አስተላልፏል።በሰላማዊ ታጋዮች ላይ ቀረበው ክስ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ነው በሚል በሰብአዊ መብት ድርጅቶች ሲተች ቆይቷል። በእስር ላይ ያሉት ጋዜጠኞች፣ ፖለቲከኞችና ጸሃፊዎች በመጪው ምርጫ ላይ ተጽእኖ ያሳርፋሉ በሚል ፍርሃት እንዲታሰሩ መደረጉን የሚጠቅሱት እነዚህ ድርጅቶች፣ መንግስት የጸረ ሽብር ህጉን ተቃዋሚዎችን ለመምቻነት እያዋለው በመሆኑ እንዲቀየር ይጠይቃሉ።

በሌላ ዜና ደግሞ የሰማያዊ ፓርቲ የአመራር አባል የሆነው ወጣት ኢያስፔድ ተስፋየ ከሚሰራበት ንግድ ባንክ ታግዷል። ኢያስፔድ ለኢሳት እንደገለጸው ህዳር 27 በአዲስ አበባ ለማድረግ ታስቦ በነበረው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ተይዞ ለ6 ቀናት ያክል በእስር ቤት ካሳለፈ በሁዋላ ፣ ወደ ስራው ሲሄድ መታገዱ ተገልጾለታል።

## ሽመልስ ከማል ከሬድዋን ሁሴን ጋር በመጋጨቱ አኩርፎ ቤት መዋል ጀመረ

ንጹሃን ኢትዮጵያዉያንን በሽብር ወንጀል ሲከስ የከረመዉና ከሦስት አመታት በላይ በየዜና ማሰራጫዉ ላይ ብቅ እያለ ወያኔዎችን ወክሎ ተራ ዉሸት ይዋሽ የነበረዉ ሽመልስ ከማል ከሌላዉ ዉሸታምና ከሃዲ ሰዉ ከሬድዋን ሁሴን ጋር ሽኩቻ ዉስጥ በመግባቱ እንዴት እደፈራለሁ በሚል ይመስል ስራዉን ትቶ ቤት ዉስጥ መዋል መጀመሩን ከወደ አዲስ አበባ የደረሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። የመንግስት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት ሚኒስትር ዴኤታ የሆነዉ ሽመልስ ከማልና ሬድዋን ሁሴን ጋር መግባባት ባለመቻላቸው ሽመልስ ከማል አኩርፎ ቤት በመቀመጥ መደበኛ ሥራውን እያከናወነ አለመሆኑን ምንጮች ገልጸዋል።

በሁለቱ የወያኔ ሎሌዎች መካከል ችግሩ የተፈጠረዉ በተለያዩ ሲሶች የተጠመደዉ ሽመልስ ከለመዳቸዉ ሱሶች ጋር በተያያዘ በመደበኛ የስራ ሰዓቱ ላይ ሊገኝ ባለመቻሉ ይህንን ባህሪውን እንዲያስተካክል በተደጋጋሚ ቢነገረዉም ሊያስተካክል ፈቃደኛ ባለመሆኑ እንደሆነ ለጉዳዩቅርበት ያላቸዉ ሰዎች ይናገራሉ። የሽመልስ ከማልን ሃላፊነት ደርቦ እየሰራ ያለዉ በቅርቡ ከዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን ዳይሬክተርነት ተነስቶ የመንግስት ኮምኒኬሽን ሚኒስትር ዴኤታ በመሆን የተሾመዉ እውነቱ ብላታ የተባለ ሰው መሆኑን ምንጮቻችን አክለዉ ገልጸዋል።

ሽመልስ ከማል በአደባባይ የታየዉ በቅርቡ በሊቀመንበርነት በሚመራዉ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቦርድ ስብሰባ ላይ ብቻ ነው። የፕሬስ ድርጅት ስራ አስኪያጅ አቶ ሰብስቤ ከበደ ከአቅም ማነስና የመልካም አስተዳደር ችግር ጋር ተያይዞ በድርጅቱ ጋዜጠኞች እየቀረበበት ያለውን ግልጽ ትችትና ቅሬታ በተደጋጋሚ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ከማስተባበሉም በተጨማሪ ጥያቄውን የሚያነሱ ጋዜጠኞችን እስከማስፈራራት የደረሰ ንግግር ሲያደርግ የተሰማዉ ሽመልስ ከማል፣ መደበኛ ስራን ትቶ ቤት የመዋሉ ጉዳይ የኮምኒኬሽን መ/ቤት የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖአል። ሽመልስ ከማል በአቶ በረከት ስምኦን ደጋፊነት የብሮድካስት ባለስልጣን ዋና ስራ አኪያጅ የነበረ ሲሆን፣ የ97 ምርጫን ተከትሎ የቅንጅት አመራሮችና ጋዜጠኞች በተከሰሱ ወቅት አቃቤ ሕግን ወክሎ ሐሰተኛ መረጃዎች እንዲቀርቡና ሐሰተኛ ምስክሮችን በገንዘብ በመግዛትና በመደለል ለኢህአዴግ ውለታ ለመስራት የጣረ ሰው መሆኑ ይታወቃል።

ይሁን እንጅ በረከት ስምኦን ከጤና ጋር በተያያዘ ስራዉን እየተዉ በመምጣታቱ ሽመልስ ከማል ብቸኛው ደጋፊዉን አጥቷል። ሽመልስ ከማል በረከት ስምኦንን የመተካት ህልም የነበረዉ ቢሆንም ቦታዉ ለሬድዋን ሁሴን መሰጠቱ የሚታወስ ነዉ። በሁለቱ ባለስልጣኖች መካከል ባለው ልዩነት የተነሳ፣ ሽመልስ ከማል ከስራው የሚባረርበት ቀን እሩቅ ላይሆን እንደሚችል ወይም በገዛ ፈቃዱ ስራውን በመልቀቅ ከአገር ለመውጣት እንደሚሞልር ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ታዛቢዎች ይገልጻሉ።

## ወያኔ ቤኒሻንጉል ጉሙዝን ለመገንጠል ተነሳስታኋል ያላቸዉን ሰለማዊ ሰዎች ለፍርድ አቀረበ

እሱ እራሱ ትግራይን ለመገንጠል ተነሳስቶ ዛሬ ኢትዮጵያን ለመምራት የበቃዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ቤኒሻንጉልን ከመገንጠል ጀምሮ የህዳሴውን ግድብ ግንባታ ለማስተጓጎል ከኤርትራ መንግስት ጋር አብራችኋላ ያላቸዉን ግለሰቦች በሽብርተኝነት ፈርጆ ፍርድ ቤት ማቅረቡን አገር ዉስጥ የሚታተወሙና አፍቃሬ ወያኔ የሆነዉ ሪፖርተር ጋዜጣ ዘገበ። በፌዴራል ዓቃቤ ሕግ ተሰናድቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 19ኛ ወንጀል ችሎት ክስ የተመሠረተባቸው አስር ተጠርጣሪዎች ላይ የቀረበዉ ክስ በመንግሥት ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ኅብረተሰቡን ለማስፈራራት፣ የአገሪቱን መሠረታዊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ሕገ መንግሥታዊና ማኅበራዊ ተቋማትን ለማናጋትና ለማፈራረስ ራሱን የቤኒሻንጉል ሕዝቦች ነፃ አውጭ ንቅናቄ (ቤሕነን) ብሎ በሚጠራው በሽብር ተግባር ላይ በተሰማራ ድርጅት ውስጥ ሆነው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር ያብራራል።

አብዱልዋሀብ መሀዲ የተባለው ተጠርጣሪ ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ ከግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን ቤሕነን የሚባለውን ሕገወጥ ድርጅት በማቋቋምና በሊቀመንበርነት ከመምራቱም በተጨማሪ፣ ኤርትራ ውስጥ ሆኖ የተለያዩ የፖለቲካ ሥልጠናዎችንና የሽብር ተልዕኮዎችን ሲሰጥ መቆየቱ በክሱ ተጠቅሷል።ተጠርጣሪው ከሌሎች ግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን ኤርትራ ውስጥ በሚገኘውና "ሀሆና" በሚባለው ወታደራዊ ማሠልጠኛ በመግባት፣ ከሁለት እስከ ስድስት ወራት ሥልጠና መውሰዳቸው በክሱ ተገልጿል። የመሣሪያዎች አጠቃቀም፣ የወታደራዊ አካል ብቃትና የፀረ ተሽከርካሪ ፈንጂ ማጥመድ ሥልጠናዎችን መውሰዳቸውንም ክሱ አክሏል። ተጠርጣሪዎቹ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጥቅምት 15 ቀን 2006 ዓ.ም. ሸርቆሌና አልቤሮ በተባሉ አካባቢዎች በሚገኘው፣ ዱምድ አቤ ተብሎ በሚጠራ መንገድ ላይ ፀረ ተሽከርካሪ ፈንጂዎችን በማጥመዳቸው፣ ጥቅምት 26 ቀን 2006 ዓ.ም. 12 ሰዎችን ጭኖ ከሸርቆሌ ወደ አስቢሮ ይጓዝ የነበረ ሚኒባስ ላይ የፍንዳታ ጉዳት በማድረስ ሦስት ሰዎች ወዲያውኑ እንዲሞቱና በዘጠኝ ተሳፋሪዎች ላይ ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስ ማድረጋቸውን ክሱ ያስረዳል።

የክልሉን መንገዶች በማጥናትና ፈንጂዎችን በማጥመድ ከፍተኛ አደጋ እንዲደርስና የንፁኃን ሰዎች ሕይወት እንዲጠፋ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ፣ ተጠርጣሪዎቹ ወደ ታላቁ የህዳሴ ግድብ የሚሄዱ ተሽከርካሪዎችን በማስቆም፣ የመከላከያ ሠራዊት አባላትንና ሌሎች ሲቪል ሰዎችን መግደላቸውን ክሱ ይገልጻል። ተጠርጣሪዎቹ ከሁለተኛው ተጠርጣሪ አብዱራህማን ናስር ከሚኖርበት ሰሜን ሱዳን በኩል በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር ደማዚን አሻራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በመገናኘት፣ የተለያዩ የሽብር ተልዕኮ ማስፈጸሚያ የጦር መሣሪያዎችን፣ ለምግብና የተለያዩ ወጪዎች የሚሆን ገንዘብ ይቀባበሉ እንደነበር ክሱ ያስረዳል። ተጠርጣሪዎቹ በሚያዚያ ወር 2006 ዓ.ም. ወደ ታላቁ የህዳሴ ግድብ የሚወሰደውን መንገድ በድንጋይ በመዝጋት፣ ከአሶሳ ከተማ ወደ ግድቡ 28 ሰዎችን ጭኖ ይጓዝ የነበረ የመከላከያ ሠራዊት ተሽከርካሪን በማስቆምና በማስወረድ፣ በአካባቢው በነበረ ጫካ ውስጥ በማስገባት፣ ሦስተኛው ተጠርጣሪ በጥይት ደብድቦ እንደገደላቸውና የያዙትን ገንዘብ እንደወሰዱ ክሱ ይገልጻል። ተሽከርካሪውንም ከራሱ ቤንዚን ስበው በማርከፍከፍ እንዳቃጠሉት ክሱ ያብራራል።

ተጠርጣሪዎቹ የሽብር ተልዕኮ ለመፈጸም ቆርጠው በመነሳታቸው በተለያዩ ጊዜያት መንገድ በመዝጋትና ተሽከርካሪዎችን በማስቆም፣ ተሳፋሪዎችን በጥይት ደብድበው በመግደል፣ እንዲሁም የተወሰኑ ሰዎችን እጃቸውን ወደኋላ በማሰር፣ በድንጋይና በዱላ በመደብደብና አንገታቸውን በመቆልመም የግድያ ወንጀል መፈጸማቸውን ክሱ ያስረዳል። የመከላከያ ሠራዊት በደረሰው ጥቆማ መሠረት ባደረገው ከበባ ለ30 ደቂቃ ያህል ተኩስ ከተለዋወጡ በኋላ ሁለት ተጠርጣሪዎች ተገድለው፣ ሌሎቹ በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ክሱ ያስረዳል። ሁሉም ተጠርጣሪዎች በተጠረጠሩበት የሽብርተኝነት ወንጀል ክስ ተመሥርቶባቸዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ሞትን ሸሽቶ ተራ ሞት ከመሞት ከገዳዮች ጋር ተፋልሞ በክብር መሞት . . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

የአንድ አካባቢ ተወላጅ የሆኑ ሰዎችን ነዉ እንጂ  ብዛት ያለዉን ሌላዉን ኢትዮጵያዊ የት ወደቀ ብለዉ እንኳን አይጠይቁም። እንዲያዉም ከቅርብ ግዜ ወዲህ ከጠ/ሚ ኃ/ማሪያም ደሳለኝን ጨምሮ ሁሉም የወያኔ ባለስልጣኖች በዉጭ አገሮች የሚኖረዉን ኢትዮጵያዊ እንደ ባዕድ መመልከና መዝለፍ ጀምረዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን አገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ አገሮች እኛ ኢትዮጵያዉያን ተገናኝተን እርስ በርስ ካልመከርንና ችግሮቻችንን በጋራ እኛዉ ካልፋታን እንደ ዜጋ የሚንከባከብልን ቀርቶ እንደ ሰብዓዊ ፍጡር የሚመለከተንም እንደሌለን ነዉ። ይህንን ደግሞ ባለፈዉ አመት ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ አሁን በቀርቡ ደግሞ የመን ዉስጥ በግልጽ አይተናል። ወገኖፐቻችን የሆኑ ኢትዮጵያዉያን የመን እንገባለን ብለዉ ቀይ ባህር ዉስጥ የአሳ ሲሳይ ሆነዉ ሲቀሩ  በጠ/ሚኒስቴርነት ስም  የወያኔ ተላላኪ የሆነዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ጭራሽ በአለም ዙሪያ የሱን እርግጫ፤ እስርና የጅምላ ግድያ ሸሽተዉ የተሰደዱ ሲትዮጵያዉያንን እጅግ በጣም አስነዋሪና አስጸያፊ በሆነ መለኩ ሲዘልፋቸዉ ተሰምቷል። የሚገርመዉ ባለፈዉ ህዳር ወር ማለቂያ ላይ ቀይ ባህር ዉስጥ ሰጥመዉ ካለቁት ከሰባ በላይ ወገኖቻችን ዉስጥ ገሚሶቹ ባለፈዉ አመት ከሳዑዲ ተባርረዉ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱና እነ ቴዎድሮስ አድሃኖም ኢትዮጵያ ለዜጎቿ የማታደርጉወ ምንም ነገር የለም ብለዉ የተናገሩላቸዉ ሰዎች ናቸዉ።

ባጠቃላይ እኛ ኢትዮጵያዉያን አገራችን ዉስጥ ተዋርደናል፤ በስደት በምንኖርባቸዉ አገሮች ዉስጥም ተዋርደናል። አገር ዉስጥ ወያኔ እንዳሻዉ ያስረናል፤ ይደበድበናል ይገድለናል። ይህንን ጠልተን ከአገራችን ስንሰደድ ደግሞ በየበረሃዉና በየባህሩ ላይ ክብርና ወግ ላለዉ ቀብር እንኳን ሳንበቃ እንደወጣን እንቀራል።  ካሁን በኋላ እንደ ህዝብ መብታችንና ነጻነታችን ተከብሮ አንደ አገር ደግሞ አንድነታችንና ዳር ድንበራችን ተጠብቆ ለመኖር የምንፈልግ ከሆነ አማራጩ አገራችንን አንደ ምጽዐት ለቅቀን መዉጣት ሳይሆን ለዚህ ሁሉ ዉርደትና መከራ ከዳረጉን ዘረኞች ጋር ፊት ለፊት መግጠምና ይለየለት ማለት ብቻ ነዉ። ወያኔ የሚፈጽምብን ሰቆቃ እንዲቆም፤ አስርና ግድያዉ አክትሞ ስደት እንዲያበቃ ብቸኛዉ አማራጭ እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ መግለጫ ማዉጣትና ከንፈር መምጠጥ ብቻ ሳይሆን የችግሮቻችንን ምንጭ ማድረቅ ነዉ፤ ወይም ዘረኛዉን የወያኔ አገዛዝና እሱ የገነባዉን ዘረኛ ስርዐት ነቃቅለን ማስወገድ ብቻ ነዉ። በዜግነታችን ተከብረንና በገዛ አገራችን ኮርተን መኖር የምንችለዉ ይህንን ስናደርግ ብቻ ነዉ።

## የግንቦቱን የምርጫ ድራማ ተከትሎ የወያኔ ሹማምንት . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አገዛዙ በምርጫ ስም በየ አምስት አመቱ ከለጋሾች ያጋብስ የነበረው ብዙ ሚሊዮን ዶላር እርዳታ መታገዱን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ለዚህም አብይ ምክንያቶች የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በዜጎች ላይ እያደረሰ የሚገኘው አፈና፡ ጭቆናና የከፋ ሰብአዊ መብት ጥሰቶች መሆናቸው ይታወቃል።

ለመጭው የግንቦት ወር ምርጫ ማስፈጸሚያንት በሚል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሪግራም (UNDP) የአውሮፓ ህብረትን ጨምሮ ከተለያዩ ለጋሾች 7.1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሰባሰብ አቅዶ ይዞ የነበረ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ምንም አይነት ድጋፍ ከለጋሾሽ እንዳላገኘ ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የፋሺስቱ ወያኔ ምርጫ ቦርድ ተብየ ምርጫ ከመቃረቡ በፊት በጀቱን ያሳውቅ የነበር ቢሆንም የዘንድሮውን አመት በጀት ግን እስካሁን ይፋ አለማድረጉ ታውቋል። የአውሮፓ ህብረትን ጨምሮ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሪግራም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ገንዘብ የሚያሰባስብባቸው እና ከአሁን ቀደም ምርጫ የታዘቡ አካላት በዘንድሮው ምርጫ በታዛቢነት እንደማይቀርቡ መገለጹ ይታወሳል።